# አማራዎች ሆይ ጉበታችን በጉሙዞች ተበልቷል ይምትሉ ስለባዎች ከኢሕአፓ ጀሌዎች ስድብ ይሰውራችሁ! (ጌታቸው ረዳ)

**Ethiopian Semay**



አማራዎች ዛሬም በአብይ መንግሥት ጊዜ መባረር መገደል ቀጥሏል።ሊሂቃኖች አብይን በማወደስ ብዕራቸው ዕርፍት አጥቷል። አማራዎች ግን ዛሬም ዕረፍት አጥተዋል። አማራ ተበድሏል፤ተገድሏል ባልን ቁጥር በእያሱ ዓለማየሁ (ሃማ ቱማ) የሚመራው ካፍንጫው ርቀት ማዶ ማየት ያቃተው ጸረ አማራው እና ጸረ ትግሬ የኢሕፓ ጀሌው ክፍል ስለ አማራ በተናገርን ቁጥር ሲያወርድብን የነበረው የስም ማጥፋት ዘመቻ እና ጎሰኛ ስድብ ታስታውሱታላችሁ። ዛሬ ኢሕአፓዎች እንዲማሩበት አንድ የቪዲዮ ማሰረጃ ይዤ ቀርቤአለሁ። እንደውም ከነዚህ የፖለቲካ ደናቁርት እና ዘረኞች ጋር ዳግም ላለመናገር ወስኜ ነበር፤ ሆኖም አንድ ወዳጄ ይህንን ቪዲዮ ልኮ ኢሕአፓዎች እንዲያደምጡት ብታደርግ ጸጸት ቢሰማቸው ስላለኝ፤ ፀፀት የሚሰማቸው ባይሆኑም ሕዝብ እንዲያውቀው ግን አደርጋለሁ ብየ ይኸየው በዚህ ርዕስ ለዳግም ጊዜ መጥቻለሁ።

ተከታታይ አንባቢዎቼ እና ገለልተኛ ታዛቢዎች እንደምታስታውሱት አማራዎች በጉሙዞች ታርደው ጉበታቸውና ኩላሊቶቻቸው መበላቱ እዛው ከአደጋው አምልጠው ምስክርነታቸውን ስቶክሆልም ከተማ ለሚገኘው ለኢትዮጵያን ራዲዮ አዘጋጆች (ኢትዮፓትርዮትስ.ካማ ድረገጽ) የሰጡት ምስክርነት በጠቀስኩት ድረገጽ ተለጥፎ ለሕዝብ መደመጡ ታስታውሳላችሁ። ይህ የሆነው አምና ነው። በወቅቱ ይህንን ዘግናኝ ስነምግባርና አገዳደል አስመልክቼ በመኮነን አንድ ጽሑፍ ማውጣቴንም ታስታውሳላችሁ። አምና የቀረበው ዘገባ በሚመለከት የአማራ ጥቃት ከመኖሪያቸው ማፈናቀል አልፎ ተገድለው ጉበታቸው እና ኩላሊታቸው እየተበላ መሆኑን እና ጥቃቱ ምን ያህል ርቀት እየተዘረጋ እንደሆነ ባቀረብኩት ዘገባ ላይ

የኢሕአፓ ጀሌዎች አሲምባ ከተባለ ድረገጽ ላይ እኔን ዋሾ ከማድረግ አልፈው የኔን ስም በማጉደፍ እና ከዚያም አልፈው በትግሬነቴ ብዙ ዘለፋ አድርሰውብኛል። የአማራ ጥቃት በመኮነኔ በኢሕአፓዎች የደረሰብኝ የስድብ ውርጅብኝ ታዛቢዎች እንድትፈርዱ የሚከተለውን ዘረኛ እና ያልተሞረደ ጹሑፋቸውን ላስታውሳችሁ እና የአማራዎች ጉበት ሲበላ በዓይኑ የተመለከተ ተፈናቃይ ለታሪክ የተዘገበ ምስክርነቱን በሕዘብ ፊትና በሚዲያ ቀርቦ የሰጠውን ቃል የተቀረጸ ቪዲዮ ይዤአችሁ እገባለሁ።

የሚከተለው ጽሑፍ መንግሥቱ የተባለ ሳንሆዜ ከተማ የሚኖር (ፋኖ፤ አደባባይ፤ አንድ ለናቱ፤ የአደራ ቃል.....በሚል በጣም በርካታ በሆኑ በብዙ የብዕር ስሞች የሚጠራ ስለ እኔም ሆነ ጉምዝ ላይ ስለተበሉ አማራዎች በሚመለከት የጻፈውን ላስታውሳችሁ እና ወደ ውይይታችን እንገባለን። እንዲህ ይላል።

“አቶ ጌታቼው እኛ ኢትዮጵያውያን አረመኔዎች አይደለንም። ፍርሃ-ዕግዚያብሄር ያለን ሕዝቦች፣ ሰውን ያኅል ፍጡር አይደለም የጋማ ከብት የማንበላ መሆናችንን እኛ አይደለንም ዓለም በሙሉ ግጥም አርጎ የሚያውቀው እውነታ ነው። ጉምዝ አማራ በላ ብለኅ ከብጤዎችህ ጋር ሁነህ በርካታ ግብዞችን ስታታልል አይተን ሰምተን ዝም አላልነም። ይህች የወያኔ የዕጅ ሥራ ናት ወገን ተጠንቀቅ ነው ያልነው። ነውናም **ጉምዝ አማራ በላ ብሎ ጉምዝን በአረመኔነት መክሰስ ዘረኝነት አይደለም ትለኛለኅ?** ታዲያ ዘረኝነትና ወያኔነት እኮ ተወራራሽ ናቸው። ናቸውናም የወያኔን ፖለቲካ ነው የምታራምደው ማለት ነው። አማራን ከጉምዙ፣ ከኦሮሞው፣ ከቅማንቱ፣ ከአገው ወዘተ ነጥሎ ለመምታት ወያኔ አዘውትሮ የሚጠቀምበትን ዘዴ አበክረን ስለምናውቅ ያኔ ነው የአንተ ነገር የገባን። ዘር ከልጓም ይስባል አይደል፣ በዕናንተ ደግሞ ይህ አዲስ ነገር አይደለም። ወያኔን ማመን ቀብሮ ነው የምንለውም ለዚያ ነው። ወያኔ ባፍ-ጢሙ ሊደፋ ሲል በ፩፩ኛው ስዓት መምጣትህና በኢ ሕ አ ፓ ላይ መዝመትኅም እንዲያው በድንገት፣ እንዲሁ በአጋጣሚ ሊሆን እንድማይችልም ሆድኅ ያውቀዋል። (ከአደራ ቃል)።

እንዲህ እየሉ ነበር ኢሕአፓዎች የአማራን ብሶት እንዳናሰማ በዘራችን እየመዘዙ ሲዘልፉን የነበሩ።

ሌላው አሲምባ ድረገጽ የተባለ ካዘጋጆቹ ዋናው የሆነው በብዕርሰ ስሙ ‘አቶ ሰውየው’ በመባል የታወቀው ሰው በማከል እንዲህ ይላል፡
“ከአማራው በላይ የአማራው ሕዝብ ተቆርቋሪ ሲሆንብን፣ እንዲያው አማራው የሚያስብ ጭንቅላት ወገን የሌለው ነው ብሎ ማን አይዞህ እንዳለው እንጃለትና” (አቶ ሰውየው አሲምባ ድረገጽ አዘጋጅ)

“አማራዎች የቤንሻንጉል ሕዝባችን ለመስደብ ሲሉ ሰው ይበላል፤ሃይማኖት የላቸውም ለማለት ነው ይህ የውሸት ወሬ እየነገሩን ያሉ” (አሲምባ ድረገጽ ኤዲቶሪያል)፡

ይህ የምስክርነት ቃል የመሰከሩትን “ወያኔዎች” ናቸው እያሉ እኛም በወያኔነት ሲከሱን እና በዘራችን ሲቆሻሹ ካየን ዱሮም ኢሕአፓ ጻፈው የተባለው ሰነድ ጸረ አማራነቱን ሰነድ ይቆጫል፤ አዎ ጽፈናል ግን ይቅርታ ይላል ብለን መጠበቅ ይቻላል። አማራዎች እየተገደሉ ጉበታቸው እየወጣ በጉሙዞች ተበልቶ አይተናል ብለው እራሳቸው አማራዎች የመሰከሩትን መለስው በወየኔነት ሲከስዋቸው አይተን ከእንግዲህ ወዲህ ከነዚህ ሰዎች ጋር የፖለቲካ ክርክር መግጠም ጊዜ ማቃጠልም ነው።  ይላል ብለን እንችላለን። ከዚህ ቀጥሎ ያለው ሰነድ ማየት ይቻላል። ይህ ደግሞ ከነማስረጃው በክፍል በክፍል ያቀረበው የአቻምየለህ ታምሩን ክርክር ወልቃይት.ካም እና ዘሓበሻ ላይ ቀርቧል። ያንን መመለክት ነው። መልስ ሊሰጡበት ቀርቶ ሰነድ አቅራቢው አቻምየለህ ለክርክር ጋብዞአቸው “አድረው ሸሱት”።እሺ ብለው ከሕዘብ ፊት ከመከራከር ይልቅ “አቻምየለህ” በጀሌዎች አጠራር “ወያኔ” ነው። በቃ መልስ ሲያጡ ስም እየለጠፉ መጓዝ ነው። ይህንን ሰነድ ተመለክቱልኝ።

ኢሕአፓ የኢትዮጵያ ችግሮች ሁሉ ምንጭ «የአማራ ማገ አህሎኝነት የወለደው የብሔር ጭቆና ነው» ካለ በኋላ በወቅቱ «የኦሮሞ ሕዝብ፣ የሶማሌ ሕዝብ፣ የአፋር ሕዝብ፣ የኤርትራ ሕዝብ፣ የትግራይ ሕዝብ፣ ወዘተ» እያደረጉ ያለውን የጸረ አማራ ማገ አህሎኝነት ትግልና የብሔር ጭቆና እስከመገንጠል ትግል እንደሚደግፍና ለዚህም «ቅዱስ ዓላማ» እንደሚታገል፤ እየታገለም እንደሆነ «የማያወላውል አቋሜ» ነው ሲል ይነግረናል። ኢሕአፓ የኢትዮጵያን ሲገልጽ «የምኒልክ የአማራ ነፍጠኞች መስፋፋት ውጤት» ይላታል። ዳግማዊ አጤ ምኒልክንም «ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር በመተባበር በአፍሪካ ምድር የሚገኙ ብሔረሰቦችን የወረረ» ይልና ምኒልክ ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር በመተባበር አፍሪካን መቀራመቱን የማያምን ካለ «ይታነቅ» እንጂ ሀቁ ያ ነው “ ይለናል።

በመጨረሻ የቪዲዮ ማስረጃውን ለማየት ከማየታችሁ በፊት የኢሕአፓ ጀሌዎች (የሃማ ቱማ ተከታዮች) ትግሬ በአማራ ላይ መናገር፤ መቆርቆር መብት የለውም፤ አያገባውም! እያለ ዘረኛ ጽሑፉን ከማስተጋባት አልፎ እኔን ብቻ ሳይሆን አማራዎች ተገድለው ጉበታቸው ሲበላ አየተናል ሲሉ የመሰከሩ ተፈናቃይ አማራዎችንም ጭምር ነው፤ **“አማራዎች የቤንሻንጉል ሕዝባችን ለመስደብ ሲሉ ሰው ይበላል፤ሃይማኖት የላቸውም ለማለት ነው ይህ የውሸት ወሬ እየነገሩን ያሉ” (አሲምባ ድረገጽ ኤዲቶሪያል)**፡ሲሉ ዘልፈዋቸዋል። እባካችሁ ማስረጃውነ ቃለ መጠይቁን እንኳ አድምጡ ብንላቸውም፤ “ካፈርኩ አይመስለሰኝ” ነበር ያሉት።

ያም ሆነ ይህ የአማራ ሰቆቃ ይፋ እንዳይሆን በኛ ላይ የሰም ማትፋት ዘመቻ ቢዘምቱብንም ስለ አማራ የምንጮህ ዜጎችንበተለያየ ዘለፋ ቢሰድቡንም ለትግላችን መነሻ ምክንየቶች ነበሩን ነበሩ፤ አሁንም አሉን። ለዚህም "አማራዎች የቤንሻንጉል ሕዝባችን ለመስደብ ሲሉ ሰው ይበላል ፤ ሃይማኖት የላቸውም ለማለት ነው ይህ የውሸት ወሬ እየነገሩን ያሉ" (አሲምባ ድረገጽ ኤዲቶሪያል)፡ የሚለው የማፈኛ ዘዴአቸውን ፈርተን የአማራው ብሶቱ ከማስተጋባት አንቆጠብም።

## <u>ታሪክ ወደ ኋላ መለስ ብለን የኢንጂኔር የሃይሉ ሻውል ምስክርነትና እሮሮ ላስታውሳችሁ፡-</u>

የተጠናከረው ጠንካራ ረዚስታንስ ቆሞ እምቢ የሚል ስለጠፋ ነው። አንድ ሰው ከቤቴ አልወጣም ሲል ሚሊሺያ መጥቶ ደብድቦ አጎሳቁሎ፤ አቁስሎ፤ ከቤቱ አስወጥቶ ሜዳ ላይ ይጥለዋል። ማን መጥቶ ይከላከልለት? መንግሥት የለ፤ የሌላ ብሔረሰብ መጥቶ አይረዳውም፤ ብቻውን አማራ የሚባለው "በሽታ ይመስል" ሁሉም ....ሌላ ቀርቶ የአገር ውስጥ የፖለቲካ ተቃዋሚዎች እንኳ ሁሉም የአማራ ጉዳይ መስማት አይፈልጉም!" በቃ እውነቱን መናገር ነው፡ አይፈልጉም! በቃ መስማት አይፈልጉም! ከመጀመሪያ ቀን ይህ መንግሥት ከመጣ ቀን ጀምሮ ይህንኑ ነው እየተደረገ ያለው። ለወር ትጮሃለህ፤ ነገሩ ተድበስብሶ እንደገና ተረስቶ ዝም ይባላል፤ ከወር በኋላ ሲከሰት እንደገና ተድበስብሶ ይታለፋል፤ እንደዛ እያለ ኮንሲስታንት/ቀጣይ/ የሆነ፤ በሕብረት የሚሰራ በውጭም በውስጥም የለም። ይህንን አይገባችሁም? "የፖለቲካ ተቃዋሚዎች እንኳ ሁሉም የአማራ ጉዳይ መስማት አይፈልጉም!" በቃ እውነቱን መናገር ነው፡ አይፈልጉም! በቃ መስማት አይፈልጉም!" (ሃይሉ ሻውል ከኢሳት ጋዜጠኛ ጋር ከመሳይ መኮነን ጋር ያደረጉት ቃለ ምልልስ)

ይህንን ስሞታና ጥሪ ሰምተን ስለ አማራ የቆምን ዜጎች "ከአማራ በላይ አማራ ለመሆን" ብላችሁ ዜጎች በዘራችን ስትሰድቡን ለታሪክ ከመተው ምን ማለት እንችላለን? እባካችሁ የአማራን ብሶት የሚጮሁም ሆነ፤ ለምስከርንት የቀረቡትንም አትዝለፉ! ለኢሕአፓ ጀሌዎች ማለት የምፈለወገው ይህንን በቪዲዮ የተቀረጸ ምስክርንት አድምጡ። አማራዎች ጉበታቸው እንደተበላ የመጨረሻው ምስክር በቪዲዮው "ስትሪም" ወደ መጨረሻ ገደማ የቀረበውን አድምጡና እንደገና መስካሪውን በወያኔነት ወይንም በትግሬነት ስም እየለጠፋችሁ፤ በለመዳችሁት ምላስ "የቤንሻንጉል ሕዝባችን ለመስደብ.... እያላችሁ አማራውን ተፈናቃይ ዝለፉት"። *("አማራዎች የቤንሻንጉል ሕዝባችን ለመስደብ ሲሉ ሰው ይበላል፤ሃይማኖት የላቸውም ለማለት ነው ይህ የውሸት ወሬ እየነገሩን ያሉ" (አሲምባ ድረገጽ ኤዲቶሪያል)፡*

ዘግናኙን ዜና ለማድመጥ ሰሞኑን የተለጠፈው ቪዲየው አድምጡ።

አማራ አሁንም ይፈናቀላል መንገኞቹ አብይ አብይ ይላሉ::
https://youtu.be/GE-atownPNs

ለአማራ ህጻናት፤ አረጋውያን እመጫቶች እና ወላጆች እህቶች እና ወጣቶች መቆም “ከአማራ በላይ ለአማራ ተቆርቋሪ መሆን የሚከጅለው” እየተባለ የሚያስሰድብ ከሆነ ‘አማራ እየተገደለ ስጋው እየተበላ ነው’’ ሲባል “በትውልድና በአፍ አማራ ሆኖ የአማራ ምስክሮችን መልሶ ውሸታሞች እያለ የሚሰድብ አማራ” በተሻለ መንገድ የአማራን ሰቆቃ ቀድሜ በማድመጤ እሰየው ቀድሜ ስለ አማራ ወገኔ መቆርቆሬ ዛሬም ለወደፊትም ያኮራኛል። ከዚህ ቪዲዮ በኋላ እውነታው ትማራለችሁ የሚል ሳይሆን ለታሪክ ግን ቪዲዮው ለአንባቢ ግንዛቤ እንዲሆን ይኼው። እንደለመደባችሁ ‘መልስ ለመስጠት ባይከጅላችሁ እና ብትሞክሩም የበለጠ ስለሚያስገምታችሁ’ ይርታ ጠይቁዩ ካልሆነም እንደ ጨዋ ልቦና ከዚህ ትምህርት ቅሰሙ።ማለት የምችለው ግን ”ኣኢተናል ብላችሁ ድርጊቱን ያጋለጣችሁ ምስክሮች ሆይ ከነዚህ ዘረኞች የሚሰነዘረው ”በወያኔነት ወይንም በትግሬነት” የስም ልጠፋ እንዳይለጠፍባችሁ ዛሬም አምላክ ይሰውራችሁ።

አማራ አሁንም ይፈናቀላል መንገኞቹ አብይ አብይ ይላሉ::
https://youtu.be/GE-atownPNs

ጌታቸው ረዳ (Ethiopian Semay)